# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE SEVEN: **ህጻኗ የት አለች?**

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ሙላቱ AT አቶ መኩሪያ RESIDENCE**

- **አቶ መኩሪያ (M, 45)**
- **ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE 2: ንጉሴ AND አቶ ጃለታ HAVE A CHAT AT THE SWIMMING POOL**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND ምህረት IN HOSPITAL**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ዶክተር አቻምየለሽ (F, 40)**
- **ሙላቱ (M, 45)**

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤  ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ ሶስት ታዳጊ ወጣቶች የየቀን ዉሎ የሚያወሳዉ የራድዮ ድራማችን ነዉ። ስለ ንጉሴ፣ ምህረት እና ዳንኤል፡፡ እነዚህ ታዳጊ ልጆች ሀገራቸው ውስጥ አሉ ከሚባሉት አንዱ በ ሆነው የቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተዋል፡፡ ግን እየተከታተሉ ያሉት ትምህርታቸውን አይደለም ፡፡ በየቀኑ ከባድ ብዙውን ጊዜ ወሳኝ የሆኑ ድምዳሜዎች ላይ ሲደርሱ እያየናቸው እየተከተልናቸው ነው፡፡ እስኪ ለማስታወስ ያህል እስከ አሁን ምን እንደሆነ መለስ ብለን እንቃኝ፡፡

የንጉሴ እናት የልጃቸው ነገር አስጨንቋቸዋል፡፡ ንጉሴ ኮምፒዩተሩ ላይ እንዳፈጠጠ ድንገት ደርሰውበት፤ የሚሰራዉን ላለማሳየት ሸፍኖባቸዋል። በመጨረሻም የንጉሴ እናት ልጃቸው ሊያይ ይችላል ይሆናል ብለው የጠረጠሩትን አሳፋሪ ነገር ለባለቤታቸው አካፍለዋል፡፡

2. ወይዘሮ ዘውዲቱ (EP 06, LINE 48): “እንዴት እንደምነግርህ ግራ ገብቶኛል፤ እ,እ, ንጉሴ ኢንተርኔት ላይ ያያል ብዬ እጠረጥራለሁ። እ,እ,,, ይመስለኛል ኢንተርኔት ላይ እራቆት ሴቶችን እያየ ነው፡፡”

3. አቶ ጃለታ: “ ምን? ፖርኖግራፊ ማለትሽ ነዉ? ንጉሴ ፖርኖ እያየ ነው? እንዴት ልታዉቂ ቻልሽ”

4. ወይዘሮ ዘውዲቱ (52): “አባቱ ነህ! እንደወንድ በግል ከተነጋገራችሁ እረጅም ጊዜ ይመስለኛል!”

የምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት ሴት ልጅ ቢገላገሉም ባለቤታቸው አቶ ሙላቱ ህጻኗን ለሌላ ሰው ለመስጠት ወስነዋል።

5. ሙላቱ (EP 05, 106): “ ሉሊት፣ ህጻኗን ስጪኝ…”
6. ወ/ሮ ሉሊት (EP 04, 39): “ አይሆንም፣ አይሆንም፣ ምን ማለትህ ነዉ፣ አይሆንም፣ ፈጽሞ አይሆንም! ሙላቱ፣ ያንን ማድረግ አትችልም! አልፈቅድልህምም!”
7. ሙላቱ (EP 04, 47): “ ህጻንዋን የሚንከባከብልን አንድ ሰው እፈልጋለሁ። ሌላ ልጅ ማሳደግ አንችልም።”
8. ሙላቱ (EP 05, 111): “ ወይዘሮ ሠዓዳ ወይም ሌላ ሰው ስለ ህጻኗ ቢጠይቅሽ ከተወለደች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መሞቷን ንገሪያቸው።።”

ወ/ሮ ሉሊት የተገላገሉትን ህጻን ባለቤታቸው አቶ ሙላቱ ይዘው ከቤት ሲወጡ በድንጋጤ ዉስጥ ነበሩ። ግን አቶ ሙላቱ ሴት ልጃቸውን ወዴት ይሆን የወሰዷት? “ ህጻኗ የት አለች?” - የዚህ የሰባተኛው ክፍል ድራማ ርዕስ ነው። አቶ ሙላቱን በከተማው ሀብታም ከሚባሉ ቤተሰቦች አንዱ በሆነው የአቶ መኩሪያ ቤተሰብ መኖርያ በር ላይ ቆመው እናገኘቸዋለን። ምን ይከሰት ይሆን? ጭዉዉቱን ተከታተሉ።

**SCENE 1: ሙላቱ AT አቶ መኩሪያ RESIDENCE**

9. **SFX: DOGS BARKING LOUDLY AT STRANGER**

10. **SFX: DOORBELL BEING RUNG SEVERAL TIMES**

11. **ሙላቱ:** (from outside gate) እንደምን ዋሉ አቶ አቶ መኩሪያ፡፡ በሩን ይከፈቱልኛል እባኮዎ? ውሻዎችዎ አፋቸውን እንዲዘጉ ይንገሯቸው እባኮዎ፡፡ እእ.....ከእንቅልፍ እኮ ፡፡

12. **SFX: GATE DOOR BEING OPENED AUTOMATICALLY**

13. **አቶ መኩሪያ:** (ordering from a little distance away) እናንተ ጅል የሆናችሁ ውሾች ዝም በሉ! እዝያ ጥጋችሁ ላይ ሄዳችሁ ተጋደሙ!

14. **SFX: DOGS MAKE SOFT NOISES AS IF SCARED, AND RUN OFF**

15. **SFX: BABY STARTS TO CRY**

16. **አቶ መኩሪያ:** (excited) አይ ፈጣሪ! ልጃችን መጥታለች! ዘበኛ፣ በሩን አንዴ ክፈተው እባክህ፡፡

17. **SFX: GATE BEING OPENED AUTOMATICALLY**

18. **SFX: FOOTSTEPS APPROACHING**

19. **አቶ መኩሪያ:** (happily) ግባ...ግባ ወዳጄ፡፡ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል፡፡ ነርሷም እየጠበቀች ናት፡፡ ባለቤቴ ቤት እንደመጣች ትረከብሃለች፡፡ ግን,,,ወንድ ነው ሴት?

20. ሙላቱ: አዝናለሁ፣ የተከበሩ አቶ መኩሪያ...ሴት ናት።

21. አቶ መኩሪያ: አዝናለሁ? ለምን ታዝናለህ? ልጅ ልጅ ነው። ልጅ ለማግኘት ከ10 አመታት በላይ ስንሞክር ያላደረግነዉ ነገር አልነበረም! ግን አልተሳካልንም። አሁን ይህ ለኛ የሚደንቅ ተአምር ነው! እስቲ አምጣት ልቀፋት እስቲ?

22. SFX: FOOTSTEPS OF TWO MEN WALKING INTO HOUSE

23. ሙላቱ: አይሆንም! አሁን አይቻልም። በመጀመሪያ ገንዘቤን እፈልጋለሁ።

24. አቶ መኩሪያ: ገንዘብህን-፣ ችግር የለም አባክህ። እቤት ነው ያለው ና ግባ፤ ግባ ወዳጄ።

25. SFX: DOOR CLOSING

26. አቶ መኩሪያ: ና እዚህ ጋር ተቀመጥ ባክህ፣ ...

27. SFX: ሙላቱ SITTING ON SOFA

28. አቶ መኩሪያ: መልካም። ይኸውልህ ገንዘብህ። 40,000 ገና ከባንክ የወጣ ጥሬ ገንዘብ። ከፈለግህ ልትቆጥረው ትችላለህ።

29. ሙላቱ: አያስፈልግም። አምኖታለሁ አቶ መኩሪያ!እ,,, ይህቻት ህጻኗ አሁን የርሶ ብቻ ናት።

30. SFX: BABY IS TAKEN BY አቶ መኩሪያ

31. SFX: BABY CRIES EVEN MORE

32. አቶ መኩሪያ: (tries to calm it down) አይዞሽ፣ የእኔ ትንሿ መልአክ፤ አሁን ይኸው አባትሽ!

33. ሙላቱ: (shouts) እንዴ ምን እያሉ ነው? አባቷ እኮ እኔ ነኝ!

34. አቶ መኩሪያ: (stern warning) አንተ ጂል አሁን ስማኝ! ከግቢዬ እንደወጣህ ይህች ልጅ በእኔ ስም መጠራት ትጀምራለች። ሀሳብህን መቀየር ከፈለክ አሁኑኑ ተናገር።

35. ሙላቱ: (apologetic) ይቅርታ፤ ሀሳቤ ሌላ ቦታ ነበር። በእርግጥ አሁን የእርሶ ልጅ ናት።

36. አቶ መኩሪያ: እና ሙላቱ ሰማህ! ባለቤትህ በዚህ እንደምትስማማ እርግጠኛ ነህ?፣ እኔ ምንም አይነት ጭቅጭቅ አልፈልግም!

37. ሙላቱ: ትስማማለች! ነግሬያታለሁ።

38. አቶ መኩሪያ: እና ልጅዋን እንደተገላገለች ወዲያውኑ ህጻኑ እንደሞተባት ትናገራለች፣ አይደል?

39. ሙላቱ: አዎ። ስምምነታችን ያ ነበር። ተደርጓል።

40. አቶ መኩሪያ: ጥሩ። ገንዘብህን ይዘህ ቤቴን ለቀህ ውጣ። ይህ በእኔ እና በአንተ መካከል ይቀራል። አለቃህ አቶ ጃለታ እንኳ ስለዚህ ማወቅ የለበትም። እርሱ የጓደኛችን ዘመድ ነው።

**41. ሙላቱ:** ልክ ነው፡፡ በዚህ ሊያምኑኝ ይችላሉ፣ አቶ መኩሪያ

**42. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: ንጉሴ AND አቶ ጃለታ HAVE A CHAT AT THE SWIMMING POOL

**43. SFX: PEOPLE SWIMMING IN A POOL**

**44. አቶ ጃለታ:** (tired from swimming) ንጉሴ! በእውነት የዋና ችሎታህ ተሻሽሎዋል፡፡ በየጊዜው ፍጥነት እየጨመርክ ነው፡፡

**45. ንጉሴ:** (also tired from swimming) አመሰግናለሁ አባ፡፡ መዋኘት ደስ ይለኛል፡፡ ወዲዚህ የቱሪስት ሆቴል መምጣታችን ትክክልኛ ውሳኔ ነው፤ እንደ አሪፍ መዋኛ ነው ያላቸዉ፡፡

**KW BEGIN**

**46. አቶ ጃለታ:** እውነትህን ነው? የምትወደው አይነት መዋኛ ነው ወይስ በመዋኛዉ ዙሪያ ሌላ ያስደሰተህ ነገር አለ?

**47. ንጉሴ:** (confused) እ,,,,ምን እንዳልክ አልገባኝም አባዬ

**48. አቶ ጃለታ:** ዙሪያህን ተመልከት! የዋና ልብስ ብቻ ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፡፡ ታድያ እነሱን ስታይ,,,እ,, ደስ አይልህም?

**49.** **ንጉሴ:** (embarrassed) አባዬ! እያሳፈርከኝ ነው። አጮልቄ የማይ መስሎህ ነዉ?

**50.** **አቶ ጃለታ:** ንጉሴ፣ ንጉሴ,,,አዳምጠኝ፤ እኔ አባትህ ነኝ። ከእኔ ካባትህ ጋር ደግሞ ግልጽ ልትሆን ይገባል።

**51.** **ንጉሴ:** በርግጥም ካንተ ጋር እኮ ግልጽ ነኝ።

**KW END**

**52. SFX: WET STEPS AROUND THE POOL**

**53. SFX: TOURIST DIVES IN SWIMMING POOL**

**54.** **አቶ ጃለታ:** (angry) ሄይ ማነህ ! መጀመሪያ እዚህ መጥተህ ሰዎች ላይ ውሃ ከማንቦጫረቅህ በፊት እንዴት ዋና ዉስጥ ዘሎ እንደሚገባ ማለቴ ዳይቭ እንደሚደረግ ተማር። (to ንጉሴ) ስማኝ ልጄ፣ ስማኝ፣ እናትህ እየተጨነቀች ናት።

**55.** **ንጉሴ:** ምንድን ነው የሚያስጨንቃት?

**56.** **አቶ ጃለታ:** ስለ አንተ ነዋ። እ... እጅ ከፍንጅ ይዤዋለሁ ብላለች?

**57.** **ንጉሴ:** (totally confused) አሁን የምትለው ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም!ስለምንድን የምታወራው አባ?

**58.** **አቶ ጃለታ:** ንጉሴ እናትህ ኢንተርኔት ላይ የሆነ አንድ ነገር ሲያይ አይቼዋለሁ ብላለች። (whispers) ፖርኖ.

**59.** **ንጉሴ:** (surprised) አባ! እየቀለድክ ነው!

**60.** **አቶ ጃለታ:** አሁን፣ አታስመስል። ይሄ በህይወትህ ወሳኝ አካላዊ እና ስሜታዊ ደረጃ እንደሆነ አውቃለሁ እናም ይህ እድሜህ ግራ የሚያጋባ እንዲህ አይነት ስሜቶችን የሚያታግልበት ጊዜ ነው። ግን ንጉሴ፣ እንደዛ አይነት ተልካሻ ነገሮች ህይወትህን ያበላሹታል...

**61.** **ንጉሴ:** ኧረ እኔ እንዲህ አይነት ነገር ፈጽሞ አይቼ አላውቅም! ኧረ እንዳውም በአዕምሮዬ ውል ብሎም አያውቅም። እውነት ነው፤ እማዬ ጠዋት ኢንተርኔት ላይ አፍጥጬ አግኝታኛለች፣ ግን ያ ስንኞችን ስፈልግ ነበር።

**62.** **አቶ ጃለታ:** ስንኝ? የመዝሙር ስንኞች?

**63.** **ንጉሴ:** (slowly coming out with the truth) እ...እንደ እሱ አይደለም። የፍቅር ደብዳቤ እንዴት እንደሚጻፍ እየፈለግኩ ነበር። ያቺን ልጅ ሲመስለኝ ሳልወዳት አልቀርም።

64. አቶ ጃለታ: (starts to realize) አሃሃ አሁን ገባኝ። የፍቅር ደብዳቤ ናሙና ነበር የምትፈልገዉ፤ እና እናትህ ያንን እንድታየው አልፈለክም። አሁን ገባኝ፣ በቃ አሁን ይህን የተነጋገርነውን እንርሳው።፣ አይደል እንዴ? ለምን ታድያ ወደ እኔ አልመጣህም? (Proudly) እኔ እኮ የፍቅር ደብዳቤዎች ንጉስ ነኝ።

65. ንጉሴ: አሀ፣ አባዬ ደግሞ አሁን ጀመረህ።

66. አቶ ጃለታ: ስማ እውነቴን ነው! እንደዚያ ባልሆን ኖሮ እናትህን የመሰለች ቆንጆ እንዴት አገኝ ነበር?

67. ንጉሴ: (changes topic) ልክ ነው፣ አባ፣ ምንም ይሁን ምን፣ አሁን እየመሸ ስለሆነ ወደ ቤታችን መሄድ ይኖርብናል።

68. MUSIC INTERLUDE

**<u>SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND ምህረት IN HOSPITAL</u>**

69. SFX: PUBLIC HOSPITAL ATMO

70. ወ/ሮ ሉሊት: (weak voice) አአአአሀ… ምህረት። ምንድን ነው?

71. ምህረት: (happily) እማ !! ወይኔ,,, እግዚአብሔር ይመስገን አሁን መናገር ቻልሽ፣ ፣ ለሰዓታት እራስሽን ስተሽ ነበር። ሀኪሞቹ ይሻላታል ብለዉኛል። ብዙ ደም ስለፈሰሰሽ ነዉ ግሉኮሱ የተሰካልሽ።

72. ወ/ሮ ሉሊት: ሀኪም,,? እንዴት ሆስፒታል ልመጣ ቻልኩ?

73. ምህረት: ምንም አታስታውሺም፣ እማዬ? ውይ እንደውም-ይኸዉልሽ ዶክተሯ መጡልሽ። ዶክተር አቻምየለሽ ይባላሉ። ዶክተር,,,-እናቴ ምን እንደተከሰተ የምታስታውስ አይመስልም። አብዳለች እንዴ? አላበደችም አይደል?

74. **SFX: FOOTSTEPS** ዶክተር አቻምየለሽ **ARRIVES**

75. ዶክተር አቻምየለሽ: አይ፣ አይደለም ምህረት፣ እናትሽ ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ እናቶች በወሊድ ወቅት ልጅ ሲሞትባቸው እንዲህ ይሆናሉ። እናትሽ በጣም በአስጨናቂ እና በከባድ ሁኔታ ውስጥ አልፈዋል።

**KW BEGIN**

76. ወ/ሮ ሉሊት: (starts to cry) ልጄን፣ የወለድኳትን ልጄን አፈልጋታለሁ።

77. ዶክተር አቻምየለሽ: እንደውም ሲያለቅሱ ይሻላቸዋል። የጠፋች ልጃቸውን እንዲረሱ ይረዳቸዋል። ግን የተወለደችዉ ልጅ ላይ ምን እንደተከሰተታውቂያለሽ?

78. ምህረት: ኧረ አላውቅም! እኔ ትምህርት ቤት ነበርኩ እና እቤት ስገባ እናቴ ብቻዋን- አዋላጅ በሌለበት፣ ወድቃ አገኘኋት አባቴም አልነበረም። እማዪ በበኩልዋ ጉዳዩን አባቴ እንደሚያብራራልኝ ብትነግረኝም ከትምህርት ቤት ከመጣሁ ጀምሮ ግን አይኑን አላየሁትም።

79. ዶክተር አቻምየለሽ: አባትሽ የት ሊሆኑ እንደሚችሉ የምታውቂው ነገር አለ?

**KW END**

80. **SFX: ሙላቱ COMES IN, PANTING FROM RUNNING**

81. **SFX: FOOTSTEPS - ሙላቱ ARRIVING**

82. **ሙላቱ:** (panting) ሰላም ለሁላችሁም። ሰላም፣ ዶክተር!

83. **ምህረት:** አባዬ፣ የት ነበርክ?

84. **ዶክተር አቻምየለሽ:** አሃ አባት እርስዎ ኖት። ጥሩ። ትክክለኛ መልሶችን ማግኘት እፈልጋለሁ። ባለቤትዎ ከወለዱ በኋላ ሁኔታቸው አሳሳቢ ሁኔታ ላይ በመዉደቁ ወደእዚህ አምጥተዋቸዋል። የተወለደችው ህጻን የት እንዳለች ማወቅ እፈልጋለሁ?

85. **ምህረት:** አባ፣ ህጻንዋ ምን ሆነች?

86. **ሙላቱ:** (acting sad) በእርግጥ …ልክ ህጻንዋ እንደተወለደች… **(fake tears)** መተንፈስ አቆመች። እና ባለቤቴን እና ቤተሰቡን ከሌላ ስቃይ ለማዳን በቀጥታ ወጥቼ ቀበርኳት። ስርዓት ያለው መቃብር እንደነበር አረጋግጥላችኋለሁ።…

87. ዶክተር አቻምየለሽ: ያ ትክክል የሆነ ስራ አይደለም፡፡ ነገሩ የሆነ ነገርን ይገልጻል፡፡ አሁን ይምጡና በቀጥታ የነገሩኝን ሁሉ ወረቀት ላይ በማሳረፍ እንዲፈርሙልኝ እፈልጋለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ የህጻን ልጅዎን ሞት በህጋዊ መንገድ መዝግበን እናስቀምጣለን፡፡ ለጊዜው ታማሚዋ በቂ እረፍት ማግኘታቸውን አረጋግጡ፡፡ አሁን ደህና የሆኑ ይመስላል፤ ቶሎ ወደ ቤትም መመለስ የሚችሉ ይመስለኛል፡፡

88. **SFX: HOSPITAL CURTAIN BEING DRAWN SHUT**

89. ሙላቱ: ምህረት፣ አመኚኝ ትንሿ እህትሽ ያለችዉ የተሻለ ቦታ ላይ ነዉ፡፡

90. **MUSIC INTERLUDE**

91. **OUTRO - NARRATOR:**

በዚሁ የዕለቱን ትምህርታዊ ድራማ ቅንብር እናጠናቅቃለን። መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘዉን ትምህርታዊ ተከታታይ የራድዮ ድራማ ቀጣይ ክፍል በማድመጥ የሚከሰተዉን ነገር ተከታተሉ ። ይህን እና ሌሎችን የበማድመጥ መማር ዝግጅቶችን ሳታደምጡ ካለፍችሁ አልያም ሌሎች ክፍሎችን በድጋሚ መከታተል ከፈለጋችሁ ድረ-ገጽ አድራሻን dw.de/lbe ላይ ታገኙታላችሁ። በዚሁ አድራሻ የዳንኤልን የቪዲዮ ዘገባ በመክፈት ታሪኩን ይከታተሉ። በድጋሚ እስክንገናኝ ድረስ ለዛሬ በዚሁ እንሰናበታለን፤ ጤና ይስጥልን!